# ና ተከተለኝ

## የመማሪያ መጽሐፍ

በቲም ግሪን የተዘጋጀ

አለመግባባት እና ተቀባይነትን ማጣት ቢኖርም

ለቤተሰቦቻቸው እና ለወጡበት ማህበረሰብ እንክብካቤ እያደረጉ ፣

በክርስቶስ እና በክርስቲያን ማህበረሰብ ውስጥ ቦታቸውን ለማግኘትና

አዲስ ሕይወት ለመገንባት ለሚጥሩ ሁሉ የተበረከተ ፡፡

# እባክዎ በቅድሚያ ይህንን ያንብቡ

*ና ተከተለኝ የመማሪያ መጽሐፍ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል ለጀመሩ ሰዎች የተዘጋጀ ትምህርት ነው። ዓላማውም አማኞች በጌታ እና በሚያምኑት መካከል ጠንክረው ማድግ እንዲችሉ መርዳት ነው።*

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ ብቻውን ሙሉ ኮርስ/ጥናት/ አይደለም፡፡ ከሦስቱ የመጀመርያው ብቻ ነው ፡፡ ስለዚህ እባክህ ይህን መንገድ ተከተል ፡፡

በመጀመሪያ ለአንድ ትምህርት የተዘጋጀውን ግለ ጥናት ጨርስ ፡፡ ( *ገፅ 3* ይህ እንዴት እንደሚደረግ ያስተምራል፡፡ )

- ከዚያም፣ ያን ትምህርተ ከአማካሪህ ጋር ወይም ከቡድንህ ጋር በመሆን ተወያይበት
- ከዚያም የተግባር ሥራውን ተለማመድ ፡፡

እነዚህ ደረጃዎች ሲጣመሩ አዕምሮህን ለመመገብ፣ ልብህን ለማቅናትና እጅህን ለተግባራዊ ስራው ያለማምዱሃል፡፡




ይህን የመማሪያ መጽሐፍ ጠቀሜታው አነስተኛ ስለሚሆን እባክዎ ለብቻዎ አያጥኑት። ይልቁኑም እንደ አማካሪ የሚረዳዎ ጥበበኛ የሆነ የክርስቶስ ተከታይን ይፈልጉ። ከእያንዳንዱ ትምህርቶች የቤት ውስጥ ጥናት በኋላ ከአማካሪዎ ጋር ይገናኙ። ምን እንደተማሩ እና እንዴት በተግባር እንደሚያውሉትም በጋራ ተወያዩበት። በህይወትዎ ስላሉ ጉዳዮችም ምክርን ይጠይቁ። በጋራ መጸለይ እና በክርስቶስም እርስ በእርስ ልንበረታታ እንችላለን።

ከሌሎች አማኞች ጋር በቡድን ብንሠራው ደግሞ ትምህርቱን የበለጠ አስደሳች ሆኖ እናገኘዋለን።

*ና ተከተለኝ ትምህርት አማካሪ ከሆኑ፤ እባክዎ የአማካሪውን መመሪያ ያግኙ። የትምህርቱም መመሪያ እንዴት ትምህርቱን መጠቀም እንዳለብን ያብራራልናል። ደቀ መዝሙር ስለማድረግ እና የቡድን ወይይትን ስለመምራት መመሪያዎችን የያዘ ነው፡ ፡ 'ባህላዊ ምልከታዎችም' በዚህ ትምህርት ውስጥ ያሉትን ርእሶች ለመረዳት ይረዱሃል። ለእያንዳንዱም ትምህርት ዝርዝር የመወያያ ጥያቄዎች አሉ። ለዚህ ደግሞ የአማካሪው መመሪያ ብዙ ሊያግዝህ ይችላል።*

# ማውጫ

ትምህርት ገጽ

እባክዎ በቅድሚያ ይህንን ያንብቡ ........ 2
የተማሪው መመሪያ ........ 4
ትምህርት 1:ይቅር መባል-የክርስቶስ ተከታይ መሆን ........ 5
ትምህርት 2: በክርስቶስ ያለ አዲስ ህይወት ........ 11
ትምህርት 3: እግዚአብሔር አባት ........ 17
ትምህርት 4: በመንፈሱ ኃይል ክርስቶስን መታዘዝ ........ 22
ትምህርት 5፣ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር /ጸሎት/ ........ 28
ትምህርት 6፣ የእግዚአብሔር ቃል ለእኛ ........ 34
የትምህርት 6: ክለሳ ........ 39
ትምህርት 7: የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አባላት ........ 40
ትምህርት 8: የሁለት ማህበረሰብ አባላት ........ 46
ትምህርት 9: የስደት ምክንያቶች ........ 52
ትምህርት 10: ለስደት ምላሽን መስጠት ........ 57
ትምህርት 11: ባሎችና ሚስቶች ........ 62
ትምህርት 12፣ ግጭቶቻችንን መፍታት ........ 69
ትምህርት 13: ምስክር መሆን ........ 77
ትምህርት 14፣ ጥምቀት ........ 83
ትምህርት 15፣ ቀጥተኛው መንገድ ........ 88
ትምህርት 16: የመውደድ ህግ ........ 94
ትምህርት 17: ጾም እና መስጠት ........ 99
ትምህርት 18: ዕጣ ፈንታ እና ምትሃት ........ 106
ትምህርት 19: የእርስ በእርስ አገልግሎት ........ 113
ትምህርት 20: መንፈሳዊ ጉዞ ወደ መንግስተ ሰማይ ........ 119
ተጨማሪ 1: ዕለት ተዕለት ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ ........ 126
ተጨማሪ 2: እንዴት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ........ 128
አስተያየትህን እንጠይቃለን! ........ 131
የትምህርት ጥያቄዎች መልስ ........ 132

# የተማሪው መመሪያ

*1.* **ወደ እዚህ ትምህርት እንኳን ደህና መጡ !** ትምህርቱም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲከተሉ በየዕለት ህይወትዎ ይረዳዎታል። እኔ የእርሶ መምህር ነኝ እናም ከትምህርቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጥቂት መመሪያዎች እዚህ ለእገዛ ቀርበዋል።



3. ይህን ትምህረት በየዕለት ህይወት ውስጥ መተግበር እጅግ አስፈላጊ ነው! እያንዳንዱም ትምህርት በቀጣይ ሳምንት <u>የሚደርጉትን</u> 'ተግባራዊ ስራ' የያዘ ነው።

2. ይህን የመማሪያ መጽሐፍ ጠቀሜታው አነስተኛ ስለሚሆን ለብቻዎ እንደ አማካሪ የሚረዳዎ ጥበበኛ የክርስቶስ ተከታይን ይፈልጉ። ከእያንዳንዱ የሳምንት ትምህርቶች የቤት ውስጥ ጥናት በኋላ ከአማካሪዎ እና በተለይም አብረው ከሚማሩ ተማሪዎች ጋር ይገናኙ።

1. እያንዳንዱ ጥያቄ በጥንቃቄ ይነበብ
2. በተዘጋጀው ባዶ ቦታ መልሰዎን ይጻፉ ወይም የ 'X' ምልክት ያስቀምጡ
3. የእርስዎን ምላሽ ካስቀመጡ በኋላ በትምህርቱ በስተመጨረሻ መልሱን ሊያመሳክሩ ይችላሉ
4. በዚህ መጽሃፍ ውስጥ የተጠቀምንባቸው ምልክቶች:

   እያንዳንዱን ትምህርት ከጨረሱ በኋላ፤ ቁልፍ ነጥቦችን ለመከለስ ቅኝት ያድርጉ

   አንዳንድ ጥያቄዎች በውይይት ጊዜ የራስዎን ግለ-አስተያየት ይዘው እንዲቀርቡ ይጠይቃሉ

5. ለመጀመሪያዎቹ አምስት ትምህርቶች የሚያስፈልግዎ ይህ የመማሪያ መጽሐፍ ብቻ ነው። ከትምህርት ስድስት ጀምሮ ግን በግል የሚጠቀሙበት መጽሐፍ ቅዱስ የስፈልግዎታል። በዚህ ትምህርት ውስጥ በአብዛኛው ኪንግ ጀምስ (KJV) እንጠቀማለን፤ ይሁን እንጂ ሌላ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ብንጠቀምም ችግር የለውም። መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ትርጓሜ ቀርቧል፤ ነገር ግን የሁሉም ጽሑፍ ከአንድ ቋንቋ ምንጭ የመጣ ነው። ምንጩም አይለዋወጥም።
6. በዓለም ዙሪያ እንደ እርስዎ ከተመሳሳይ ሃይማኖት የመጡ ብዙ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች አሉ። አንዳንዶች በትምህርት የላቁ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ያልተማሩ ናቸው። ይህም ትምህርት ዝቀተኛ ትምህርት እንኳን ያላቸው ሰዎች እንዲረዱት ተደርጎ በቀላል መንገድ የተጻፈ ነው። ምንአልባትም የማስተማሪያ ዘዴውን እጅግ ቀሎ አግኝተውት ይሆናል፤ ነገር ግን በህይወትዎ ለመታዘዝ ፈቃደኛ ነዎት? እግዚአብሔር ከአዕምሯዊ ዕውቀታችን ይልቅ መታዘዛችንን ይፈልገዋል። ትምህርቱንም የምንታዘዝ ከሆነ ማትረፊያ ይሆንልናል።
7. ያስታውሱ፤ አማካሪዎ እርሶዎን ለመርዳት የራሳቸውን ጊዜ ሰጥተዋል። በእያንዳንዱ የውይይት ጊዜ በሰዓት በመድረስ እና የቤት ስራዎን አጠናቀው በመምጣት ለአማካሪዎ ያሎትን አክብሮት ያሳዩ።

ከዚህ በኋላ በትምህርት ውስጥ ባለቤት ሆኖ በነጠላ ቁጥር "አንተ" ስለምንጠቀም ይህን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡልን።

**አሁን፤ በጌታ እርዳታ እንጀምር!**

# ትምህርት 1:ይቅር መባል-የክርስቶስ ተከታይ መሆን

## የህይወታችን ዓለማ



ሁለት ሰዎች ውይይት ያደርጉ ነበር። አንደኛውም ሰው "ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር ትዕዛዛቱን እንደጠብቅ እንደፈጠረኝ አምናለው። ነቢያቱንም ቀጥተኛውን መንገድ እንዲያሳዩኝ ልኳል። ያቺንም መንገድ የምከተል ከሆነ እግዚአብሔር ኃጢያቴን ይቅር ይለኛል እናም ወደ ገነትም እገባለው ብዬ ተስፋ አደርጋለው። የህይወት ዓላማዬ ይህ ነው።" አለ። ሁለተኛውም ሰው "እኔም የእግዚአብሔርን ትዕዛዛቱን መጠበቅ እፈልጋለው። ነገር ግን ወደ ገሀነመ-እሳት ይልከኛል ብዬ አልፈራም። ኃጢያቴን ይቅር ብሎኛል እና በሰማይም እንኳን ደህና መጣ ሊለኝ ቃል ገብቶልኛል። ስለዚህ፣ በዚህ ምድር በግሌ ስለተዋወኩት ደስ ይለኛል፣ የእርሱ ፍቅር ይሰማኛል እና እኔም እወደዋለው። በየዕለቱ በእያንዳንዱ ቅጽበት ለእርሱ መኖርን እፈልጋለው። የህይወት ዓላማዬ ይህ ነው።" ብሎ መለሰ።




1. ለእኛ ስለ ህይወታችን ማሰብ እንደ ሸክም ነው። የዛሬ ችግሮቻችን እና ስለወደፊቱ ያለን ጭንቀት እጅጉን ይጫኑናል። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሁላችን የሚሆን ድንቅ ተስፋን በቅዱስ ቃሉ (ኢንጂል) ሰጥቶናል።

"እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ።" ማቴ 11፥28

ኢየሱስ ክርስቶስ በግሉ ይህን ቃል እንደተናገረው ሰው ሆነህ አስብ! በቃል ማለት እስከምትችል ድረስ አሰላስለው። ከዚያም ባዶ ቦታውን ሙላ

"እናንተ ________፣__________________ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ።"

2. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ቃል የተናገረው ወደ እዚህ ዓለም በመጣ ጊዜ ነበር። ሰዎችን "ና፣ ተከተለኝ" ብሎ ይጠራ ነበር። ጥቂቶቹም በደስታ የእርሱ ተከታይ በመሆን ምላሽን ይሰጡ ነበር። ሌሎች ደግሞ አልተቀበሉትም። ዛሬም ክርስቶስ ህያው ነውና ለእኛም ተመሳሳይ ግብዣን ይጠራናል። "ና፣ ____________"

### የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ መሆን

3. የክርስቶስ ተከታይ እንዴት መሆን እንደሚቻል እንማር። ከክርስቶስ የመጀመሪያ ተከታዮች መሃከል የነበረውን ዓሳ አጥማጁ ስምዖን ጴጥሮስን እንደ ምሳሌ መከተል እንችላለን። ከመጽሐፍ ቅዱስም ስለዚህ እናንብብ

ሕዝቡም የእግዚአብሔርን ቃል እየሰሙ ሲያስጠብቡት ሳሉ፥ እርሱ ራሱ በጌንሳሬጥ ባሕር ዳር ቆሞ ነበር፤ በባሕር ዳርም ቆመው የነበሩትን ሁለት ታንኳዎች አየ፤ ዓሣ አጥማጆች ግን ከእነርሱ ውስጥ ወጥተው መረቦቻቸውን ያጥቡ ነበር። ከታንኳዎቹም የስምዖን ወደ ነበረች ወደ አንዲቱ ገብቶ ከምድር ጥቂት ፈቀቅ እንዲያደርጋት ለመነው፤ በታንኳይቱም ተቀምጦ ሕዝቡን ያስተምር ነበር።
ነገሩንም ከጨረሰ በኋላ፥ ስምዖንን፦ ወደ ጥልቁ ፈቀቅ በል መረቦቻችሁንም ለማጥመድ ጣሉ አለው። ስምዖንም መልሶ፦ አቤቱ፥ ሌሊቱን ሁሉ አድረን ስንደክም ምንም አልያዝንም፤ ነገር ግን በቃልህ መረቦቹን እጥላለሁ አለው።

ይህንም ባደረጉ ጊዜ እጅግ ብዙ ዓሣ ያዙ፤ መረቦቻቸውም ተቀደዱ። በሌላ ታንኳም የነበሩትን ጓደኞቻቸውን መጥተው እንዲያግዙአቸው ጠቀሱ፤ መጥተውም ሁለቱ ታንኳዎች እስኪሰጥሙ ድረስ ሞሉአቸው። ስምዖን ጴጥሮስ ግን ባየ ጊዜ በኢየሱስ ጒልበት ላይ ወድቆ፦ ጌታ ሆይ፥ እኔ ኃጢአተኛ ነኝና ከኔ ተለይ አለው። ስላጠመዱት ዓሣ እርሱ ከእርሱ ጋርም የነበሩ ሁሉ ተደንቀዋልና፥ እንዲሁም ደግሞ የስምዖን ባልንጀሮች የነበሩ የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስም ተደነቁ። ኢየሱስም ስምዖንን፦ አትፍራ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ሰውን የምታጠምድ ትሆናለህ አለው። ታንኳዎችንም ወደ ምድር አድርሰው ሁሉን ትተው ተከተሉት። ሉቃስ 5፣1-11

ሁሉንም አንብበህ ከጨረስህ፣ የ (X) ምልክትን በሳጥን ውስጥ ☐ አስቀምጥና ቀጥል።

4. ስምዖን ጴጥሮስ የኢየሱስ ተከታይ ለመሆን አራት እርምጃዎችን የወሰደ ይመስላል። በነዚህ አራት እርምጃዎች ዛሬም ሰዎች የጌታ ኢየሱስ ተከታዮች ይሆናሉ። ስለእነርሱም አሁን እንማራለን።

## የመጀመሪያው እርምጃ፡ ከኃጢያት መመለስ

ስምዖን የዓሳውን ታምራት ባየ ጊዜ፣ አይኖቹ ተከፈቱ። ከራሱም አፍረት ጋር በማነጻጸር የጌታ ኢየሱስ ቅድስናን ተረዳ፥ ፡ ለኢየሱስም ያለው ምን ነበር? "ጌታ ሆይ፥ እኔ ________________ ነኝና ከኔ ተለይ አለው።"

5. ስምዖን 'ኃጢያተኛ ሰው' እንደሆነ ተገነዘበ። ምንአልባትም የማንንም ነፍስ አላጠፋም ወይም ዝሙት አልፈጸመም። ነገር ግን ኢየሱስ ልቡን ማየት ይችል ነበር። ስምዖንም ከጌታ ኢየሱስ አሳፋሪ ሚስጥሩን ወይም ክፉ ሃሳቡን መደበቅ አይችልም ነበር።

አንተስ? የአንተ የተደበቁ ሚስጥሮች ምንድናቸው፣ በአካባቢ ከሚኖር መስጊድ በድምጽ ማጉያ ከፍ ባለ ድምጽ ቢነገር ከሃፍረት የተነሳ ለሞት የሚያበቁ? ይህን ሚስጥር ምንአልባትም ከጎረቤትና ቤተሰብ መደበቅ ችለህ ይሆናል ነገር ግን ከኢየሱስ ክርስቶስ መሸሸግ አይቻልም። የህክምና ባለሙያ በኤክስ ሬይ እያንዳንዱ የተሰወረ የሰውነታችን አጥንቶችን እንደሚያይ እርሱም በህይወታችን የተደበቀውን ክፉ ግልጽ ሆኖ ያየዋል።

➢ ቆም በል፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በህይወትህ ያሉ የጨለማ ጥጎችን እንዲያሳይህ ጠይቀው።

6. በእርግጥም ሰው ሁሉ በኃጢያት ተበላሽቷል። ገጣሚው ኡመር ከዩም እንዳለው

"በዚህ ዓለም ኃጢያት ያልሠራውን ንገረኝ
ኃጢያት የለሾቹ የት እንዳሉ ንገረኝ
በአንተ ሰቼ እናም አንተ አስተኸኝ
እስቲ የኔን እና አንተን ልዩነት ንገረኝ።"

ከእግዚአብሔር ኃጢያቱ/ቷ/ን መደበቅ የሚችል አለ? [አዎ/የለም]

7. ከዚህ ቀደም እግዚአብሔር ንጹሐንን እንደሚወድ እና ስህተት የሚሠሩትን እንዴት እንደሚጠላ ተምረሃል። ነገር ግን ንጹሁ ኢየሱስ ያልነጻውን ስምዖንን ጠልቶ ነበርን? በሚገርም ሁኔታ አልነበረም! ኢየሱስ ለስምዖን ያለው ምን ነበር?

ሀ. 'ከእኔ ራቅ' ለ. 'አትፍራ'

8. ከኢየሱስ ‘አትፍራ’ የሚለውን መስማት ለስምዖን ምን ያህል እረፍት ነበር! አንተም እንደስምዖን ከሆንክ ዕድፋም ኃጢያተኛ ሰው እንደሆንክ አስተውል። መሲሁ ኢየሱስ አንተን ይቅር ሊልህ እና ከኃጢያት ሁሉ ሊያነጻህ ዝግጁ ነው፥ ፤

እነዚህን ተነጻጻሪ ሁለት ሰዎች ተመልከት፥







**ኢምራን** **ሻፊ**

ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያነጻው የትኛውን ዓይነት ሰው ነው፥ እንደ ኢምራን ያለ ኩሩ ሰውን ነው ወይስ እንደ ሻፊ ያለ ትሁት ሰውን ነው? ____________________

9. ጌታ ኢየሱስም “ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም አላቸው።” ሉቃ 5፥32 ‘ንስሐ’ ማለት የጉዞ አቅጣጫን በመቀየር የሚደረግ ምልስነት ነው። እነዚህ ሁለት ሰዎችን ተመልከቱ



1. 2.

__________ ሀ. ንስሐ የገባው ሰው ይትኛው ነው 1 ወይስ 2?

__________ ለ. በቀድሞ መንገዱ የቀጠለውስ የትኛው ነው 1 ወይስ 2?

10. ‘ንሰሐ መግባት’ በኃጢያታችን ከመጸጸት ያለፈ ነው። ይህውም ከኃጢያት ሙሉ በሙሉ በስዕል ቁጥር 2 ላይ እንዳለው ሰው መመለስ ማለት ነው። ስለዚህ የእውነተኛ ንስሐ ማስረጃው የቱ ነው?

__________ ሀ. በኃጢያት ለቆሸሸ ህይወት ጸጸት የለሽ መሆን

__________ ለ. በኃጢያት መጸጸት ነገር ግን የህይወት ዘይቤን አለመቀየር

__________ ሐ. ሙሉ በሙሉ ከኃጢያት መመለስ እና የህይወት ዘይቤን መቀየር

11. ስምዖን የኢየሱስ ተከታይ ለመሆን የወሰደው የመጀመሪያ እርምጃ ምን ነበር? ከ ____________ መመለስ ነበር።

## ሁለተኛ እርምጃ፥ ዋጋውን መረዳት

12. ለስምዖን ቀጠይ እርምጃው የክርስቶስ ተከታይ መሆን የሚጠይቀውን ዋጋ መረዳት ነበር። ስምዖን ከባድ ምርጫ ከፊቱ ቀርቧል። ምንአልባትም በሁለት ሃሳቦችም ተይዟል፤




ስምዖን የተረዳው ምን ነበር? የክርስቶስ ተከታይ መሆን የሚጠይቀውን ________________::

13. ኢየሱስ ክርስቶስ የእርሱ ተከታይ መሆን ምን ያህል ዋጋን እንደሚያስከፍል የህን ምሳሌ ተናግሯል።

> "ደግሞ መንግሥተ ሰማያት መልካምን ዕንቁ የሚሻ ነጋዴን ትመስላለች፤ ዋጋዋም እጅግ የበዛ አንዲት ዕንቁ በአገኘ ጊዜ ሄዶ ያለውን ሁሉ ሸጠና ገዛት።" ማቴዎስ 13: 45 -46

እንደ ኢየሱስ ተከታይ፣ መተው ያለበህ ዋጋን የሚያስከፍሉ ነገሮች ምንድናቸው? ከሚከተሉት ውስጥ የአንተ የሆነውን አንድ ወይም ከዚያ በላይ ምረጥ፤

________ሀ. በማህበረሰቡ ውስጥ ያለህ ተቀባይነት

________ለ. የተቀጠርክበት ስራ ወይም ንግድህ

________ሐ. ቤተሰብህ

________መ. ንብረትህ ወይም ውርስ

ሠ. ሌሎች (እዚህ ጻፈው) ______________________

14. 'ዋጋው እጅግ የበዛ ዕንቁ' ግን ግምቱ ነው! ስለክርስቶስ ምንም ዓይነት መስዋዕት ብንከፍል፣ እርሱ ስለእኛ በመስቀል ላይ ታላቅ መስዋዕትን እንደከፈለ ልብ ልንለው ይገባል።

> ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል። ሮሜ 5፡8

ስለዚህ ታላቁን ዋጋ የከፈለ ማነው፣ እኛ ወይስ ክርስቶስ? ______________________

በትምህርት 9 እና 10 ስደትን ለመግጠም እንዴት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚረዳን እንማራለን።

## ሦስተኛ እርምጃ፡ ራስን ለክርስቶስ መስጠት

15. ስምዖን የክርስቶስ ተከታይ ለመሆን፤ በመጀመሪያ ከኃጢያቱ ተመለሰ፣ በሁለተኛ ደረጃ የሚጠይቀውን ዋጋ ተረዳ፡ ፡ በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ 'ራሱን ለክርስቶስ ሰጠ'
በጥያቄ 3 በምንባቡ ውስጥ ያለውን የመጨረሻ አረፍተ ነገር አንብብ። ስምዖን እና ጓደኞቹ ለኢየሱስ ጥሪ ምላሻቸው ምን ነበረ?

"ታንኳዎችንም ወደ ምድር አድርሰው፣ ____________________ _____________________።"

16. ስምዖን በአዲሱ ጌታው፣ ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ራሱን ሰጥቶ ነበር። በየዕለቱ ህይወታችን ምን ያህል ራሳችንን ለሌላ አሳልፈን እንሰጣለን? ጥቂት ምሳሌዎችን እንይ፡

- ✓ የደከመው ህጻን ወደ አባቱ እጆች ሲዘልል እንደሚያቅፈው በመተማመን ነው።
- ✓ ህመምተኛ መድኃኒት የሚወስደው ሀኪሙን ተማምኖ ነው።
- ✓ የአውቶብስ ተጓዥ በአደገኛ ጉዞ ላይ የሚሄደው አሽከርካሪውን ተማምኖ ነው።

ልክ እንደዚህ ህጻን፣ ታማሚ ወይም ተሳፋሪ፤ በኢየሱስ እጅ ላይ ራስችንን ስናስቀምጥ እርሱን ተማምነን ነው። እንዲጠብቀን እና እንዲመራን እንታመነዋለን። እንደ ጌታችንም እንታዘዘዋለን።

የክርስቶስ ተከታይ በመሆን ሦስተኛው እርምጃ ምንድነው?

1. ከኃጢያት መመለስ
2. ዋጋውን መረዳት
3. ራስን ለክርስቶስ ___________________________

17. ለክርስቶስ ራሱን ከሰጠ በኋላ፣ ስምዖን ጴጥሮስ ከእርሱ ጋር ለሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት አብሮት ተጉዟል። የጌታውን ደስታ እና ሀዘን ተካፍሏል። ኢየሱስ ህሙማንን ሲፈውስ እና ሙት ሲያስነሳ አይቷል። ኢየሱስ ሰውን እንደወደደ እንዴት ሰውን እንዲወድድ ተምሯል። ቀስ በቀስ ለማጅ ተማሪው ስምዖን መምህሩ ኢየሱስን ይበልጥ ወደ መምሰል መጣ። በኋላም ጴጥሮስ በሚለው ሁለተኛ ስሙ በብዛት ይታወቅ ነበር።
ስምዖን ጴጥሮስ የክርስቶስ ተከታይ የሆነው እንዴት ነው?

ሀ. ራሱን ለክርስቶስ በመስጠት

ለ. አዲሱ እምነቱን በቃል በመድገም (ካሊማ ወይም ሽአዳ)

18. እንደሚታወቀው፣ ለማጅ ተማሪ በምልከታ እና በቅጂ ከመምህሩ ይማራል። እንደ ኢየሱስ 'ለማጅ ተማሪ' ወይም 'ደቀመዝሙር' ስምዖን ጴጥሮስ ያደገው እንደዚህ ነበር። እኛም ጌታ ኢየሱስን ስንከተል እንደ ለማጅ ተማሪ ነው የምንሆነው። ምንም እንኳን በስጋዊ ዓይናችን ባናየውም፣ እርሱ የሰራውን እንድናደርግ ተምረናል እናም እንደእርሱም እንሆናለን። በስራውን ተካፋይ እንድንሆን ማዕረግ አለን።
የክርስቶስ ደቀመዝሙር ለመሆን ሦስተኛው እርምጃ ምንድነው? ራስን ለክርስቶስ ___________________

**አራተኛ እርምጃ፡ ከአማኞች ጋር ህብረት ማድረግ**



19. ስምዖን ለኢየሱስ ጥሪ ምላሽ በሰጠ ጊዜ፣ ብቻውን አልነበረም፡ ፡ የአማኞች ህብረትንም ተቀላቀለ። እንደ ክርስቶስ ደቀመዝሙር በአንድነት እና ህይወታቸውን በመካፈል ይኖሩ ነበር። እነርሱም ከተለያየ ጎሳ እና ከተለያየ የማህበረሰብ ክፍል የተወጣጡ ነበሩ። ይሁን እንጂ እርስ በእርስ መዋደድን የተማሩ ነበሩ። ይህ ቀላል አልነበረም። አንዳንዴ በመሃከላቸው ክርክር ነበረ። ነገር ግን ጠባቸውን በመፍታት ይቅር ይባባሉ ነበር። ስምዖን ጴጥሮስ የክርስቶስ የሆኑት ሁሉ የግድ _____________________ ማድረግ እንዳለባቸው ተምሯል፡ ፡ **ለእያንዳንዱ አማኝ የክርስቶስ ማህበረሰብን መቀላቀል አስፈላጊ ነው! በትምህርት 7 ላይ የበለጠ እንማራለን።**

20. ኢየሱስ ክርስቶስ ስምዖን ጴጥሮስ የእርሱ ተከታይ እንዲሆን ጠርቶታል። ይህም የሚያካትታቸው አራት እርምጃዎች ምንድናቸው?

i) ከኃጢያት ______________________

ii) ዋጋውን ______________________

iii) ራስን ለክርስቶስ ______________________

iv) ከአማኞች ጋር ______________________

በመጨረሻም፣ የዛሬው ትምህርት ለአንተ በግለህ ምን ትርጉምን ይሰጥሃል?

- የክርስቶስ ተከታይ ምንአልባትም ልትሆን ትችላለህ! ከሆነም ይህ ትምህርት በክርስቶስ ማደግህን እንድትቀጥል ይረዳሃል።
- ክርስቶስን ለመከተል ምንአልባትም ተዘጋጅተህ ይሆናል! ስለዚህ በግለህ ከአማካሪ ጋር አውራ እናም አማካሪህ ይህን እርምጃ እንድትወስድ ይረዳሃል።
- ስለዚህ አስፈላጊ እርምጃ ምንአልባትም ለማሰብ የበለጠ ጊዜ ፈልገህ ይሆናል! መልካም ግን ውሳኔህ ለዘላለም የዘገየ አይሁን፣ አንደ ቀን ከረፈደ ሊሆን ስለሚችል፡ ፡ ከፈለግህ ይህን ትምህርት ማጥናትህን ቀጥል ነገር ግን የበለጠ አትራፊ የምትሆነው ክርስቶስን ለመከተል ከወሰንክ በኋላ ነው።



**የትምህርት 1 ተግባራዊ ስራ**

በዚህ ሳምንት፣ ለብቻህ ቦታን አዘጋጅ እና ስለእነዚህ ጥያቄዎቹ በጥንቃቄ አስብ። የክርስቶስ ተከታይ ሆነሃል? ወይስ የእርሱ ተከታይ ለመሆን ተዘጋጅተሃል? ወይስ ለማሰብ የበለጠ ጊዜ አስፈልጎሃል?

**የትምህርት 1 ክለሳ**

1) ከማቴዎስ 11፡28 የምተረዳው ድንቅ የአየሱስ ክርስቶስ ግብዣ ምንድነው?

"እናንተ ___________፣______________________ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ።"

2) የክርስቶስ ተከታይ መሆኛ አራት እርምጃዎችን ጥቀስ

1. ከኃጢያት ______________________
2. ______________________
3. ራስን ______________________
4. ከአማኞች ጋር ______________________

# ትምህርት 2፡ በክርስቶስ ያለ አዲስ ህይወት

የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው የእምነት አንቀጽ ብቻ አነብናቢ አይሆንም። ይልቁንም በክርስቶስ የሆነ አዲስ ህይወትን ይቀበላል። ይህም

ሀ. አዲስ ማንነትን

ለ. አዲስ ውልደትንና

ሐ. አዲስ ባህሪን ያካትታል።



1. ስለዚህ አስደናቂ አዲስ ህይወት ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከሆነው 'ከአንደኛ የጴጥሮስ መልእክት' እንማራለን። በትምህርት አንድ ላይ የተማረነው ስምዖን ጴጥሮስ በእግዚአብሔር ምሪት ይህን መልእክት ጽፎታል። መልእክቱም የሚጀምረው እንደዚህ ነው፡-

   "የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ጴጥሮስ፥" (1ጴጥሮስ 1፡1)

   ጴጥሮስ የአገልግሎቱ መጠሪያ ምን ነበር? ትክክለኛ መልስ ላይ ምልክት አስቀምጥ።

   ______ ሀ. ደቀ-መዝሙር ______ ለ. ሐዋሪያ ______ ሐ. ነብይ

2. በመጽሐፍ ቅዱስ፣ 'ሐዋሪያ' ማለት ለተለየ ስራ የተላከ ሰው ነው (ቅዱስ መጸሐፍ የወረደበትም ሰው አይደለም)። ጌታ ኢየሱስ አስራ ሁለቱን መረጠ፣ አስለጠናቸው እናም ለልዩ ስራ ላካቸው። 'ሐዋሪያት' መባላቸውም ለዚህ ነው። የእነርሱም መሪ ሐዋሪያው ጴጥሮስ ነበር።
   በዚህ ትምህርት ውስጥ የምናጠናው የእግዚአብሔር ቃል ክፍል የቱ ነው? አንደኛ የሐዋሪያው ________________ መልእክት

3. አንደኛ ጴጥሮስ ቁጥር 1 ላይ መልእክቱን ማን በእግዚአብሔር ምሪት ሆኖ እንደጻፈው ይነግረናል። የመልእክቱንም ተቀባዮች ይነግረናል። እነርሱም አሁን ቱርክ ተብሎ በሚጠራው ሀገር የሚኖሩ የክርስቶስ ተከታዮች ነበሩ። በክፍሉም "በእግዚአብሔር የተመረጡ ህዝቦች" ተብለው ተጠርተዋል።

   - **እስቲ እዚህ ጋር ቆም ብለን በእርሱ የተመረጡ ህዝቦች ስላደረገን እግዚአብሔርን እናመስግነው!**

4. እዚያው ቁጥር ላይ ምጻተኞች ይላቸዋል። ምንአልባት ከትውልድ ሀገርህ ርቀህ ትኖር ይሆናል። ወይም በሀገርህ እየኖርክ ምንአልባትም በተቃውሟቸው ምክንያት ከቤተሰቦችህ ተለይተሃል። ይህም በጣም ከባድ ገጠመኝ ነው!
   በእግዚአብሔር ዕይታ ግን፣ ያለን አዲስ ማንነት ምንድነው? እኛ 'በእግዚአብሔር የተመረጡ ________________' ነን።

## ሀ. አዲሱ ማንነታችን

5. አዎ እኛ "በእግዚአብሔር የተመረጡ ህዝብ" ነን! ቀድሞ የነበርንበት ማህበረሰብ ሊቃወመን ይችላል ነገር ግን *"እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?... እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል?"* (ሮሜ 8፡31 ፣ 33) *"እግዚአብሔር እንኪያስ ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮኹ ለሚታገሣቸውም ምርጦቹ አይፈርድላቸውምን?"* (ሉቃስ 18፡7)
   እንደ ክርስቶስ ተከታዮች አዲሱ ማንነታችን የቱ ነው?
   ሀ. በእግዚአብሔር የተመረጡ ህዝብ ለ. አረመኔዎች ሐ. ከዳተኞች

*6.* የሚቀጥለው ቁጥር *"እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ እንዳወቃቸው"* (1ጴጥሮስ 1፡2)

| |
|---|
| ታሪኩ እውነተኛ ወላጆቹን ስላጣ ልጅ ይነግረናል። ሌሎች ጥንዶችም እንደ ራሳቸው ልጅ በማደጎነት አሳደጉት። አንድ ቀንም ሌሎች ልጆች በዚህም ጉዳይ ቀለዱበት። እርሱም "አይደለም፣ ከእናንተ ይልቅ ክብረት ይሰማኛል። አባታችሁ እናንተን አልመረጠም የእኔ አባት ግን እንደ ራሱ ልጅ አድርጎ መርጦኛል!" ብሎ መለሰ። |

በእግዚአብሔር *መመረጥ* የተለየ ክብር ነው! ይህም በስራችን የተገባን ነውን? [አዎ / አይደለም]

7. እግዚአብሔር የመረጠን ስለሚወደን እንጂ ስለተገባን አይደለም። በእውነትም እግዚአብሔርን በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ለመከተል መርጠናል። የእግዚአብሔር ምርጫ እና የእኛ ምርጫ በተወሰነ መልኩ በአብሮነት ይሠራል።

በክርስቶስ ያለን አዲሱ ማንነታችን ምንድነው? እኛ በእግዚአብሔር ________________ህዝብ ነን።



## ለ. አዲሱ ውልደታችን

8. በትል እና በአባጨጓሬ መሃል ያለውን ልዩነት ታውቃለህ። ምንም እንኳን የሚመሳሰሉ ቢመስሉም በመሀከላቸው ግን ትልቅ ልዩነት አለ። ትል እስኪሞት ድረስ ያለምንም ለውጥ እየተሳበ በዙሪያው ይንቀሳቀሳል። አባጨጓሬ ግን በሚደንቅ ለውጥ ውስጥ ያልፋል። በመሞት ፋንታ ምን ይሆናል?

9. በቅጠል ላይ የሚሳበው፣ አስቀያሚው አባጨጓሬ ወደ ሰማይ ከፍ ብሎ የሚበር ቢራቢሮ ሆኖ መለወጡ የሚያስደንቅ አይደለም? አዲስ ፍጥረት ለመሆን የተደረገ ሙሉ 'አዲስ ውልደትን' ይመስላል።

በአባጨጓሬ ላይ የተካሄደው ለውጥ ምንድነው? ' አዲስ __________________' የሚመስል ነው።

10. አንተ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ ሆነሃል? ከውጪ ራስህን በመስታወት ስትምለከት፣ የምታየው ከዚህ በፊት የነበረውን ያንኑ ሰው ነው። በውስጥ የሚኖረው ለውጥ ግን ልክ አባጨጓሬ ወደ ቢራቢሮ እንዳደረገው ለውጥ ታላቅ የሆነ ነው። ይህ በክርስቶስ የሆነ አስደናቂ ለውጥ 'አዲስ ውልደት' ይባላል።

አዲስ ውልደት የሚሆንላቸው ሰዎች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. በሀገራችን ያሉ ሰዎች ሁሉ

ለ. ራሳቸውን ለክርስቶስ የሰጡ ሰዎች ሁሉ

ሐ. በክርስትና እምነት ተከታይ ቤተሰቦች መሐል የተወለዱ ሁሉ

11. ስለዚህም አዲስ ውልደት በ 1ኛ ጴጥሮስ ላይ ያለው ቀጣይ ቁጥር ይነግረናል

| |
|---|
| "ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ ለሕያው ተስፋና ለማይጠፋ፥ እድፈትም ለሌለበት፥ ለማያልፍም ርስት እንደ ምሕረቱ ብዛት ሁለተኛ የወለደን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፤" 1 ጴጥሮስ 1፡3 |

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ መሠረት፣ አዲስ ውልደትን የሚሠጠን ማነው?

_______ሀ. እግዚአብሔር፣ እንደ ምህረቱ ብዛት

_______ለ. እኛ፣ በመልካሙ ስራችን

_______ሐ. ቅዱሳን በሚያደርጉልን ጸሎት

**አዲስ ውልደት ሆኖልሃል?**

12. እግዚአብሔር አዲስ ውልደትን ለሰው ሁሉ አዘጋጅቷል ሁሉ ሰው ግን አይቀበለውም። የህ ሐኪም ለሦስት ታካሚዎች የሚላቸውንና የእነርሱን ምላሽ ተመልከቱ።




ከሦስቱ ታካሚዎች የሚሻለው የቱ ነው? ________________________

13. ከዚህ በታች ከቀረቡት ሦስት ሰዎች መሃከል በክርስቶስ አዲስ ውልደትን የሚቀበለው የትኛው ነው?

_______ሀ. "ክርስቶስ ሆይ በትምህርትህ አምናለው፣ ነገር ግን በህይወቴ ልቀበልህ እፈራለው" የሚል

_______ለ. "አንተን አላምንህም" የሚል

_______ሐ. "ጌታ ኢየሱስ አንተን አምናለው። አሁን ራሴን ለአንተ እሰጣለው። ወደ ህይወቴም ግባ" የሚል

> ስለአንተስ የሚገልጸው የቱ ነው- ሀ፣ ለ ወይስ ሐ? ራስህን እስካሁን ለክርስቶስ አልሰጠህ እንደሆነ፣ እባክህ ከአማካሪህ ጋር ለብቻችሁ ተነጋገሩበት። ከዚህም በኋላም ያለው ትምህርት ይህንን እርምጃ እንደወሰድክ ታሳቢ ያደረገ ነው።



**ሐ. አዲሱ ባህሪያችን**

14. እንደ ክርስቶስ ተከታዮች ስለ አዲሱ ማንነታችን እና አዲሱ ውልደታችን ተምረናል። ኢየሱስ ክርስቶስ የእሱ የሆነ "አዲስ ባህሪንም" በእኛ ውስጥ አኑሯል።
ቀደሞ ከነበርክበት ሃይማኖት አንተ የክርስቶስ ተከታይ እንደሆንክ እነርሱም የሆኑ ብዙዎች አሉ። እርሱም በህይወታቸው ስላደረገው አዎንታዊ ለውጥ ጥቂቶቹ እንዲህ ብለው ይናገራሉ፡-

**ታሊብ፡** "በክርስቶስ ያለ ህይወት የሚደንቅ እና የሚያረካ ነው"

**ሀሰን፡** "ኢየሱስ ደስታና ሠላም ሰጥቶኛል"

**ሻሚም፡** "ጭንቀት እና ሀዘኔ ጠፋ"

**ሰዓዳ፡** ሸክም እና ፍርሃቴ ለቆኛል

**ሌና፡** እግዚአብሔር እኔን እንደ እኔነቴ እንደተቀበለኝ አውቃለው

**አህመድ፡** ያለፈ ታሪኬ፣ ቀለመ ጥቁር እና ሸታ ያለው የአልኮል መጠጥ፣ ሴሰኝነት እና ኃጢያት ነበር።

(በራልፍ ዋተን ከተጻፈው 'ከነብይ የሚበልጠው ኢየሱስ' የተወሰደ)

እነዚህ ሁሉ አውነተኛ ሰዎች ናቸው። በህይወታቸው የመጣው ልዩነት ምንድነው?

________ ሀ. ኢየሱስ ክርሰቶስ አዲስ ባህሪን ከብዙ አዎንታዊ ለውጦች ጋር ሰጥቷቸዋል።

________ ለ. ህይወታቸው ከቀድሞ የባሰ ነበር

________ ሐ. ከድሮ ባህሪያቸው በምንም አልተለወጡም

15. ኢየሱስ ክርስቶስ የእርሱ የሆነ አዲስ ባህሪን ለእነዚህ ተከታዮቹ ሁሉ ሰጥቷቸዋል። እኛም እንደእነሱ የደስታ እና የሠላም ስሜትን እንለማመዳለን። ስሜቶቻችን ግን በጣም አስፈላጊው ነገር አይደለም። በጣም አስፈላጊው ነገር ኢየሱስ በባህሪያችን ላይ የሚያመጣልን ለውጥ ነው። እስቲ ቀጥለው ያሉትን እውነተኛ ምሳሌዎች እንይ፡

**ሀሰን፡** “የማጨስ ሱሴን እንድሰብር ኢየሱስ አስችሎኛል”

**ጃንጊር፡** “የቀድሞ ትዕቢታዊ ዕይታዬን ኢየሱስ ለውጦልኛል”

**ራዛቅ፡** “ስናገር የምንተባተበው እና የዝቅተኝነት ስሜቴ ጠፋ”

**ሰይድ፡** “በጥባጭ መሆኔን አቁሜያለው”

**ሻሚም፡** “ስለሌሎች የበለጠ ማሰብን ጀምሬያለው”

**ፓርዌዝ፡** “በህይወቴ የነበረ የኩራት እና የትዕቢት ቦታ በማገልገል መንፈስ ተወስዷል።”

**ማሪያ፡** “ሌሎች የክርስቶስን ፍቅር አውቀው እንዲመጡ እጓጓለው”

በራልፍ ዋተን ከተጻፈው ‘ከነብይ የሚበልጠው ኢየሱስ’ የተወሰደ)

በአንተ ህይወት ክርስቶስ ያመጣው ትክክለኛ ለውጦች ምንድናቸው? ሃሳብህን ጻፍ እና በውይይትም ጊዜ ለማካፈል ተዘጋጅ______________________________________________________________________

16. ከላይ የተዘረዘሩትን ለውጦች ወዲያውኑ በህይወትህ አልተለማመድህ እንደሆነ አትጨነቅ። በክርስቶስ እያደግህ ስትሄድ ቀስ በቀስ ይመጣሉና ነው። ለአንድ ህጻን ልጅ አዋቂ ሰው ለመሆን ብዙ ዓመታትን እንደሚወስድ ሁሉ፤ አዲስ ውልደትን ከተቀበልን በኋላ የበሰለ መንፈሳዊ ሰው ለመሆን በተመሳሳይ መልኩ ብዙ ዓመታትን ይወስዳል።
ኢየሱስ በውስጥ በመኖሩ፣ በአንተ ላይ የበለጠ የሚታየው ‘ባህሪ’ የትኛው ነው?

_______ ሀ. የቀድሞ ኃጢያታዊ ባህሪክ    _______ ለ. በክርስቶስ ያለህ አዲስ ባህሪ

## መንፈሳዊ ውጊያችን

17. በክርስቶስ አዲስ ባህሪ ያለን ቢሆንም፣ በየቀኑ በቀረው ህይወታችን የቀድሞ ባህሪያችንን በመቃወም መንፈሳዊ ውጊያን ልናደርግ ይገባል! የእግዚአብሔርም ቃል ይህንን ትዕዛዝ ይሰጠናል፡

“እንግዲህ በምድር ያሉቱን ብልቶቻችሁን ግደሉ፥ እነዚህም ዝሙትና ርኵሰት ፍትወትም ክፉ ምኞትም ጣኦትንም ማምለክ የሆነ መጎምጀት ነው፤ … አሁን ግን እናንተ ደግሞ ቍጣንና ንዴትን ክፋትንም፥ ከአፋችሁም ስድብን የሚያሳፍርንም ንግግር እነዚህን ሁሉ አስወግዱ፤ እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፥ አሮጌውን ሰው [ባህሪ] ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና፥የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው [ባህሪ] ለብሳችሁታል፤” ቆላስይስ 3፥ 5 -10

ከላይ በተቀመጠው ጠቅስ መሠረት

ሀ. የትኛውን ባህሪ ነው መግፈፍ ያለብን?    [አሮጌውን ባህሪ/ አዲሱን ባህሪ]

ለ. የትኛውን ባህሪ ነው መልበስ ያለብን?    [አሮጌውን ባህሪ/ አዲሱን ባህሪ]

18. ከታች የቀረቡት ምስሎች የክርስቶስ ተከታዮች የተለያዩ ነገሮችን ሲሰሩ ያሳዩናል።




19. ከእያንዳንዱም ሰዎች ስር ባለው ባዶ ቦታ ላይ እንደሚያሳዩት ባህሪ 'አሮጌ' ወይም 'አዲስ' በማለት አስቀምጥ፡

ሀ. ___________ ባህሪ ለ. ___________ ባህሪ ሐ. ___________ ባህሪ መ. ___________ ባህሪ

20. የኢየሱስ የሆነውና በእኛ ያለው፣ አዲሱ ባህሪያችን በየዕለቱ ከቀደሞው ኃጢያታዊ ባህሪያችን ጋር ውጊያን ያደርጋል። ይህን ውጊያ አንድ ገበሬ፡ "ጥቁር እና ነጭ የሆኑ፣ ሁለት ፍየሎች በህይወቴ ውስጥ ሲጣሉ ይሰማኛል" ሲል ገለጸው። አድማጩም "ታዲያ የትኛው ፍየል አሸነፈ?" ሲል ጠየቀው። "በደንብ የቀለብኩት ነዋ" ሲል መለሰለት።

- **ስለገበሬው ምሳሌ አሰላስል። ጥቁሩ ፍየል የእኛን አሮጌ ባህሪ ይወክላል፤ ነጩ ፍየል ደግሞ አዲሱ ባህሪያችንን ይወክላል። በአሁን ሰዓት በህይወትህ እያሸነፈ ያለው የትኛው ነው? ለምን? ለውይይት ራስህን አዘጋጅ**



እስቲ ከዛሬው ትምህርት፣ በክርስቶስ ስላለን ሦስት ታላቅ ዕድሎች እናስታውስ፡

- በእግዚአብሔር እንደተመረጠ ህዝብ <u>አዲስ ማንነት</u> አለን
- አባ ጨጓሬ ቢራቢሮ እንደሚሆነው <u>በአዲስ ውልደት</u> ውስጥ አልፈናል
- በክርስቶስ እርዳታ፣ <u>አዲሱ ባህሪያችን</u> ቀስ በቀስ ኃጢያተኛው አሮጌውን ባህሪያችንን ይተካዋል

21. ቀጥሎ የተቀመጠው የእግዚአብሔር ቃል ዛሬ የተማርነውን በአጭሩ ያጠቃልለዋል፡



"ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።" 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17

ጥቅሱን በቃልህ ማለት እስክትችል ድረስ ባዶ ቦታውን እየሞላህ ደጋግመው፡

"ስለዚህ ማንም _____________ ቢሆን ________ ፍጥረት ነው፤ ___________ ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም ___________ ሆኖአል።" 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17

አሁን ይህንን ጸልይ፡

*"ጌታ ሆይ፣*

*በታላቅ ምህረትህ በአንተ የተመረጠ ህዝብ ስላደረከን አመሰግንሃለው!*

*አዲስ ውለደትን እና አዲስ ባህሪን ስለሰጠኸኝ አመሰግንሃለው።*

*በክርስቶስም ኃይል፣ በየዕለቱ አሮጌውን ኃጢያተኛ ባህሪ በመቃወም*

*መንፈሳዊ ውጊያን እንዳደርግ እርዳኝ። አሜን"*



**የትምህርት 2 ተግባራዊ ስራ**

ከአዲሱ ባህሪይ የተነሳ በህይወትህ የመጡ ሦስት አዎንታዊ ለውጦችን ግለጽ። ስለእነዚህ ለውጦች እግዚአብሔርን አመስግን። እስከ አሁን በህይወትህ የሚገዳደሩህን የአሮጌው ባህሪያት ሦስት ልምዶች ግለጽ። በዚህም ሳምንት እነዚህን መጥፎ ልምዶች በእግዚአብሔር እርዳታ ተዋጋ።

**የትምህርት 2 ክለሳ**

1. ሀ. ሰው ራሱን ለክርስቶስ ሲሰጥ፣ በህይወቱ የሚከሰተው ለውጥ ምንድነው? __________ ውልደት
   ለ. እንደ ክርስቶስ ተከታዮች ያለን አዲስ ማንነት ምንድነው? እኛ በእግዚአብሔር ______________ ________________ ነን።
2. መንፈሳዊ ውጊያችን በ[አሮጌው/አዲሱ] ኃጢያታዊ ባህሪያችን እና በክርስቶስ በሆነው [አሮጌው/አዲሱ] ባህሪያችን መከከል ነው። (የተሳሳተውን መልስ አውጣ)
3. ኢየሱስ ክርስቶስ በተከታዮቹ ህይወት የሚያመጣውን ሁለት የለውጥ ምሳሌዎች አስቀምጥ። (ጥያቄ ቁጥር 11 እና 12ን አመሳክር) ____________________________________________________________
4. 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17 በማስታወስ ባዶ ቦታውን ሙላ፡ "ስለዚህ ማንም ______________ ቢሆን ________ ፍጥረት ነው፤ ___________ ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም ___________ ሆኖአል።"